ትንቢተ ናሆም (Nahum)

ምዕራፍ 1።

1፤ ስለ ነነዌ የተነገረ ሸክም፤ የኤልቆሻዊውየ ናሆምየ ራእዩ መጽሐፍ ይህ ነው።

2፤ እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር ተበቃይና መዓትን የተሞላ ነው፤ እግዚአብሔር ተቃዋሚዎቹን ይበቀላል፥ ለጠላቶቹምቀጣሚን ይጠብቃልና።

3፤ እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፥ ኃይሉምታላቅ ነው፥ በደለኛውንምም፡ ንጹሕ ነህ አይልምና፤ እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ወስጥ መንገድ አለው፥ ደመናምየእግሩ ትቢያ ነው።

4፤ ባሕሩንምይገሥጻታል፥ ያደርቃትማል፥ ወንዞችንምሁሉ ያደርቃል፤ ባሳንና ቀርሜሎስምላልተዋል፥ የሊባኖስምአበባ ጠውልጎአል።

5፤ ተራሮችምከእርሱ የተነሣ ታወኩ፥ ኮረብቶችምቀለጡ፤ ምድርና ዓለምየ ሚኖሩበትምሁሉ ከፊቱ ተናወጡ።

6፤ በቀጣውፊት የሚቆምማን ነው? የቁጣውንምትኩሳት ማን ይታገሣል? መዓቱ እንደ እሳት ይፈስሳል፥ ከእርሱምየተነሣ ዓለቶች ተሰነጠቁ።

7፤ እግዚአብሔር መልካምነው፥ በመከራ ቀንምመሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ የሚታመኑትንምያውቃል።

8፤ ስፍራዋን ግን በሚጥለቀልቅ ጎርፍ ፈጽሞያጠፋታል፥ ጠላቶቹንምወደ ጨለማያሳድዳቸዋል።

9፤ በእግዚአብሔር ላይ የምታስቡት ምንድር ነው? እርሱ ፈጽሞያጠፋል፥ መከራምሁለተኛ አይነሣም።

10፤ እርስ በእርሳቸውእንደ ተመካቅለ እሾህ ቢሆኑ፥ በመጠጣቸውምቢሰከሩ እንደ ደረቅ ገለባ ፈጽመው ይጠፋሉ።

11፤ በእግዚአብሔር ላይ በክፉ የሚያስብ፥ ክፋትን የሚመክር፥ ከአንተ ዘንድ ወጥቶአል።

12፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ኃይለኞችና ብዙዎች ቢሆኑ እንዲሁ ይቈረጣሉ፥ እርሱምያልፋል። እኔም አስጨንቄሃለሁ፥ ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ አላስጨንቅህም።

13፤ አሁንምቀንበሩን ከአንተ እሰብራለሁ፥ እስራትህንምእበጥሳለሁ።

14፤ እግዚአብሔርምከስምህ ማንምከእንግዲህ ወዲህ እንዳይዘራ ስለ አንተ አዝዞአል፤ ከአምላኮችህ ቤት የተቀረጸውንና ቀልጦየተሠራውን ምስል አጠፋለሁ፤ አንተምየተጠቃህ ነህና መቃብርህን እምላለሁ።

15፤ እነሆ፥ የምስራችን የሚያመጣሰላምንምየሚያውራ ሰውእግር በተራሮች ላይ ነው! ይሁዳ ሆይ፥ አጥፊው ፈጽሞጠፍቶአልና፥ ከእንግዲህምወዲህ በአንተ ዘንድ አያልፍምና ዓመት በዓሎችህን አድርግ፥ ስእለቶችህን ክፈል።

ምዕራፍ 2።

1፤ የ ሞቃጠቅጥ በአንተ ላይ ወጥቶአል፤ ምሸግን ጠበቅ፥ መንገድን ምሰልል፤ ወገብህን አጽና፥ ኃይልህንም እጅግ አበርታ።

2፤ ዘራፊዎች ዘርፈዋቸዋልና፥ የ ወይናቸውን ምአረግ አጥፍተዋልና እግዚአብሔር የ ያዕቆብን ክብር እንደ እስራኤል ክብር ይመልሳል።

3፤ የ ኃያላኑ ጋሻ ቀልቶአል፥ ጽኑዓንም ቀይ ልብስ ለብሰዋል። እርሱም በሚዘጋጅበት ቀን ሰረገሎች እንደ እሳት ይንቦገቦጋሉ፤ የ ጦሩም ሶሞ ይወዛወዛል።

4፤ ሰረገሎች በመንገድ ላይ ይነ ጐዳሉ፥ አደባባይም ይጋጫሉ፤ መልካቸውእንደ ፋና ነ ው፥ እንደ መበረቅም ይከንፋሉ።

5፤ መሳፍንቱን ያስባል፤ በአረማመዳቸውይሰናከላሉ፤ ፈጥነ ውበቅጥርዋ ላይ ይወጣሉ፥ ማጠቢያም ተዘጋጀለት።

6፤ የ ወንዞቹም መዝጊያዎች ተከፈቱ፥ የ ንጉሥቤትምቀለጠች።

7፤ ንግሥት ተገ ለጠች፥ ተሚከችም፥ ሴቶች ባሪያዎችዋምእንደ ርግብእየ ጮኸና ደረታቸውን እየ መቱ ዋይ ዋይ ይላሉ።

8፤ ነ ነ ዌ ግን ከዳሮ ዘመን ጀምራ እንደ ተከማቸ ውኃ ነ በረች፤ አሁን ግን ይሸሻሉ፤ እነ ርሱም፡ ቁሙ ቁሙ ይላሉ፥ ነ ገር ግን የ ሚሞላስ የ ለም።

9፤ መዝገ ብዋ ሜጪሻ የ ለወፃና፥ የ ከበረ ወፃየ ዕቃዋ ሁሉ ብዛ ት አይቁጠርምና ብሩን በዝብዙ፥ ወርቁንም በዝብዙ።

10፤ ባዶና ባድማምድረ በዳምሆናለች፤ ልብ ቀልጦአል፥ ጕልበቶችምተብረከርከዋል፤ በወገ ብምሁሉ ሕማም አለ፥ የ ሰዎችምሁሉ ፊት ጠቁሮአል።

11፤ የ አንበሶችምመደብ፥ የ አንበሶችምደቦል የ ሚኖሚብት፥ አንበሳወና አንበሳይቱ ግልገ ሉምሳይፈሩ የ ሚሬዳት ስፍራ ወዴት ነ ው?

12፤ አንበሳውለልጆቹ የ ሚቃወን ነ ጠቀ፥ ለእንስቶቹምሰበረላቸውዋሻወን በንጥቂያ፥ መደቡንምበቅሚያ ሞልቶታል።

13፤ እነ ሆ በአንቺ ላይ ነ ኝ፥ ይላል የ ሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ሰረገሎችዋንምአቃጥዬ አጠፋለሁ፥ ሰይፍም የ አንበሳ ደቦሎችሽን ይበላቸዋል፤ ንጥቂያሽንምከምድር አጠፉለሁ፥ የ ሚልከተኞችሽን ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ አይሰሙ።

ምዕራፍ 3።

1፤ ለደምከተማወዮላት! በሀለንተናዋ ሐሰትና ቅሚያ ሞልቶባታል፤ ንጥቂያ ከእርስዋ አያልቅም።

2፤ የ አለንጋ ድምፅ ፥ የ መንከራከርምድምፅ ፥ የ ፈረሶችምኮቴ፥ የ ፈጣን ሰረገላምጩኸት ተሰምቶአል፤

3፤ ፈረሰኛውይጋልባል፥ ሰይፍምይንቦገቦጋል፥ ጦርምይብለጨልጫል፤ የተገደሉትምይበዛሉ፥ በድኖችም በከምር ይከሚሉ፥ ሬሳቸውምአይቈጠርም፤ በሬሳቸውምይሰናከላሉ።

4፤ ስለ ተዋበችውጋለሞታ ግልሙትና ብዛት ይህ ሆኖአል፤ እርስዋምበመሞትዋ እጅግ በለጠች፥ አሕዛብንም በግልሙትናዋ፥ ወገኖችንምበመሞትዋ ሸጠች።

5፤ እነሆ፥ በአንቺ ላይ ነኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታእግዚአብሔር፥ ልብስሽን በፊትሽ እገልጣለሁ፤ ኀፍረተ ሥጋሽንምለአሕዛብ፥ ነወርሽንምለመንግሥታት አሳያለሁ።

6፤ ርኩሰትንምበላይሽ እጥላለሁ፥ እንቅሻሻለሁ፥ ሚገጫምአደርግሻለሁ።

7፤ የሚያይሽምሁሉ ከአንቺ ሸሽቶ። ነነዌ ባድማሆናለች፤ የሚለቅስላትስ ማን ነው? የሚጽናናትንስ ከወዴት እፈልጋለሁ? ይላል።

8፤ አንቺ በሚኖች መካከል ከተቀማሽውም፥ ውኃምበዙሪያዋ ከነበራት፥ ምሽግዋምባሕር ከነበረ፥ ቅጥርዋም በባሕር ወስጥ ከነበረ ከኖእ አሞን ትበልጫልሽን?

9፤ ኢትዮጵያና ግብጽ የሚቈጠር ኃይልዋ ነበሩ፤ ፉጥና ልብያ ረዳቶችዋ ነበሩ።

10፤ እርስዋ ግን ተሟርካ ፈለሰች፤ ሕፃናቶችዋ በመንገድ ሁሉ ራስ ላይ ተፈጠፈጠ፤ በከበርቴዎችዋምላይ ዕጣ ተጣጣሉ፥ ታላላቆችዋምሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ።

11፤ አንቺምትሰክሪአለሽ ወራዳምትሆኛለሽ፤ አንቺ ደግሞከጠላት የተነሣ ማጠቢያን ትፈልጊአለሽ።

12፤ አምላሽ ሁሉ የመጂሚያወን የበሰለ ፍሬ እንደ ያዙ እንደ በለስ ዛፎች ነው፤ ቢወዛወዝ በሚላውአፍ ወስጥ ይወድቃል።

13፤ እነሆ፥ በመካከልሽ ያሉ ሕዝብሽ ሴቶች ናቸው፤ የአገርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ፈጽሞተከፍተዋል፥ እሳትም መወርወሪያዎችህን በልቶአል።

14፤ ከብበውያስጨቈሻልና ውኃን ቅጂ፤ አምላሽን አጠንክሪ፤ ወደ ጭቃገብተሽ እርገጪ የጡቡን መሥሪያ ያገቡ።

15፤ በዚያ እሳት ይበላሻል፥ ሰይፍ ያጠፋሻል፥ እንደ ደንቢያ ይበላሻል፤ እንደ ደንቢያ ብዛቱ እንደ አንበጣምተባዝቡ።

16፤ ነጋዴዎችሽን ከሰማይ ከዋክብት ይልቅ አበዛሽ፤ ደንቢያ ተዘረጋ፥ በረረም።

17፤ በአንቺ ዘንድ ዘወድየጫት እንደ አንበጣ አለቆችሽምእንደሚቀሳቀሱ ኩበኩብዎች ናቸው፤ በብርድ ቀን በቅጥር ወስጥ ይቀመጣሉ፥ ፀሐይምበወጣች ጊዜ ያከብካሉ፤ ስፍራቸውብየት እንደ ሆነ አይታወቅም።

18፤ የአሦር ንጉሥሆይ፥ እረኞችህ አንቀላፍተዋል፤ መኳንንቶችህምዐርፈዋል፤ ሕዝብህምበተራሮች ላይ ተበትኖአል፥ የሚሰበስበውምየለም።

19፤ ስብራትህ አይፈወስም፥ ቀስልህምከፉ ነ ው፤ ወሬህንምየ ሚሰሙሁሉ እጃቸውን በአንተ ላይ ያጨበጭባሉ፤ ክፋትህ ሁልጊዜ ያላለፈችበት ሰውማን ነ መና?